ቤተ መጻሕፍት

# ዘሚልክያስ ነቢይ

## መቅድም

ሚልክያስ፡ ማለት፡ መልአክ፤ አንድም፡ ሐዋርያ፡ ማለት ነው፤ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ይሳኮር፡ ነው፤ አባቱ፡ ፋሄል፤ እናቱ፡ ጽግኒ፡ ይባላሉ፤

ይህም፡ መጀመሪያ፡ ካህናቱን፡ ይዘልፋል፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ተረፈ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕለ፡ እስራኤል፡ በእደ፡ መልአኩ፤

እግዚአብሔር፡ በአሕዛብ፡ ከማ ናገር፡ የቀረው፡ በሚልክያስ፡ ቃል፡ በእስራኤል፡ ያናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፡ ይህ፡ አርእ ስት፡ ነው፤ ሠለስቱ፡ ምእት፡ ለመጻሕፍት፡ አርእስት፡ ሲሰጡ፡ ለዚህም፡ አርእስት ሰጥተውታል፤

፪፤ ሀልይዎኬ፡ በልብክሙ፡ ዘከመ፡ አፍቀርኩክሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እንደወደድኋችሁ፡ በልቡናችሁ፡ እወቁት፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

ወእመሰ፡ ትብሉኒ፡ በእንተ፡ ምንት፡ አፍቀርከነ፤

እንድትወደን፡ በምን፡ እናውቀ ዋለን፡ ብትሉ፤

አኮኑ፡ ኤሳው፡ እኁሁ፡ ለያዕቆብ፤

ኤሳው፡ የያዕቆብ፡ ወንድም፡ አይደለም?

፫፤ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ያዕቆብሃ፡ አፍቀርኩ፡ ወኤሳውሃ፡ ጸላዕኩ፤

እግዚአብሔር፡ ያዕቆብን፡ ወደ ድሁ፡ ኤሳውን፡ ጠላሁ፡ ያለ፡ አይደለም?

ወአማሰንኩ፡ በሐውርቲሁ፤

አገሩንስ፡ ያጠፋሁ፡ አይደለም?፤

ወመክፈልቶ፡ ረሰይክዎ፡ በድወ፤

ዕጣውን፤ አገሩን፡ ምድረ፡ በዳ፡ ያደረግሁት፡ አይደለም?

፬፤ እስመ፡ ይቤ፡ ናሁ፡ ወድቀት፡ ኤዶምያስ፤

ኤዶምያስ፡ ጠፋች፡ ብኋልና፤

ንትመየጥ፡ ወንሕንፅ፡ መዝበራ፤

እሷን፡ ወደ፡ መሥራት፡ እን መለስ፡ አሉ፤

ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ ሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

አንትሙሰ፡ ተሐንፅዋ፡ ወአነ፡ እነሥታ፤

እናንተ፡ ትሠሯታላችሁ፤ እኔ፡ አፈርሳታለሁ፤



ወትሰመይ፡ ብሔረ፡ ዓመፃ፤

ሀገረ፡ ግፍ፡ ትባላለች፤

፭፤ ወይሬእያ፡ አዕይንቲክሙ፡ ሕዝበ፡ ዘሠርዓ፡ እግዚአብሔር፡ እስከ፡ ለዓለም፤

እግዚአብሔር፡ የፈጠራቸው፡ እስራኤልን፡ ዓይኖቻችሁ፡ ለዘ ለዓለም፡ ያያሉ፤

ወትብሉ፡ አንትሙ፡ ዓቢይ፡ እግዚአብ ሔር፡ በላዕለ፡ በሐውርተ፡ እስራኤል፤

በእስራኤል፡ አገር፡ ላይ፡ እግዚ አብሔር፡ ገናና፡ ነው፡ ትላላ ችሁ፤ ተዓውቀ፡ እግዚአብሔር፡ በይሁዳ፡ ትላላችሁ፤

፮፤ ወልድኒ፡ ያከብር፡ አባሁ፤

ልጅ፡ አባቱን፡ ያከብራል፤

ወገብርኒ፡ ይፈርህ፡ እግዚኦ፤

አገልጋይም፡ ጌታውን፡ ይፈራል፡ ትላላችሁ፡ ትች፡ ነው፤

እመሰኬ፡ አቡክሙ፡ አነ፡ አይቴ፡ ዘአክበርክሙኒ፤

እኔ፡ አባታችሁ፡ ከሆንሁ፡ የአከበ ራችሁኝ፡ ማክበር፡ ወዴት፡ አለ?

ወእመኒ፡ እግዚእክሙ፡ አነ፡ አይቴኑ፡ ዘፈራህክሙኒ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ ሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤ ጌታችሁ፡ ከሆንሁ፡ እኔን፡ የፈራችሁኝ፡ መፍራት፡ ወዴት፡ ነው?

እስመ፡ አንትሙ፡ ካህናት፡ አርኰስ ክሙ፡ ስምየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ እናንት፡ ካህ ናት፡ ስሜን፡ አስነቀፋችሁ፡ ብኋልና፤

ወትቤሉ፡ በምንትኑ፡ አርኰስነ፡ ስመከ፤

ስምህን፡ በምን፡ አስነቀፍን፡ ትሉኝ፡ እንደሆነ፤

፯፤ እስመ፡ ወደይክሙ፡ ውስተ፡ ምሥዋዕየ፡ ኅብስተ፡ ርኩሰ፤

ከምሥዋዕ፡ ዓባር፡ የመታውን፡ እንክርዳዱን፡ አቀረባችሁ፤

ወትቤሉ፡ በምንትኑ፡ አርኰስናሁ፤

በምን፡ አስነቀፍነው፡ ትሉኝ፡ እንደሆነ፤

እስመ፡ ትብሉ፡ ማዕደ፡ እግዚአብሔር፡ ኅውር፡ ውእቱ፤

የእግዚአብሔር፡ ማዕድ፡ አስነ ዋሪ፡ ነው፡ ትላላችሁና፤

ወእክሉሂ፡ ዘሥሩዕ፡ ውስቴቱ፡ ምኑን፡ ውእቱ፤

በፊቱ፡ የተዘጋጀ፡ እህሉም፡ አባር፡ የመታው፡ እንክርዳድ፡ ነው፡ ትላላችሁ፤

፰፤ እስመ፡ ታበውኡ፡ ነቋረ፡ ለመ ሥዋዕት፤

ለመሥዋዕት፡ ዕውሩን፡ እንካሳ ውን፡ እንስሳ፡ ታመጣላችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢኮነ፡ ሠናየ፡ ከማሁ።

ዕውሩን፡ አንካሳውን፡ ማቅረባ ችሁ፡ መልካም፡ አይደለም።

ወእመሂ፡ አምጻእክሙ፡ ሐንካሰ፡ ወድ ውየ፡ ኢኮነ፡ ሠናየ።

ዕውሩን፡ አንካሳውን፡ ብታመ ጡት፡ መልካም፡ አይደለም። አን ድም፡ ብታመጡትም፡ ዕውሩን፡ አንካሳውን፡ ነው።

ሰድ፡ እስኩ፡ ለመልአክከ፡ ለእመ፡ ይት ሜጠወከ።

ይህን፡ እስቲ፡ ለንጉሡ፡ እጅ፡ መንሻ፡ አድርገህ፡ ስጠው፡ ይቀበ ልህ፡ እንደሆነ?

ወለእመ፡ ያደሉ፡ ለገጽከ፡ ይቤ፡ እግዚ አብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ ይህን፡ ተቀብሎ፡ ያዳላልህ፡ እንደሆነ፡ እስቲ፡ ወስ ደህ፡ ስጠው። እኔም፡ ይህን፡ ተቀብዬ፡ አደላላችሁ፡ እንደሆነ፤

፱፤ ወይእዜኒ፡ ተጋነዩ፡ ለገጸ፡ እግዚ አብሔር፡ አምላክክሙ።

የቀደመውን፡ ጥላችሁ፡ የፈጣ ሪያችሁን፡ ገጽ፡ ረድኤቱን፡ ለማ ግኘት፡ ተገዙ።

ወሰአልዎ፡ እስመ፡ በእዴክሙ፡ ተገ ብረ፡ ዝንቱ።

ይህ፡ ኃጢአት፡ በናንተ፡ እጅ፡ በናንተ፡ ቃል፡ ተደርጓልና፡ ለምኑት፤

ወትሬእዩ፡ ለእመ፡ አደሉ፡ ለገጽክሙ።

ይህን፡ ተቀብዬ፡ አደላላችሁ፡ እንደሆነ፡ ታያላችሁ፤

ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

፲፤ እስመ፡ በእንቲአክሙ፡ ተዓ ዕወ፡ ኆኅት።

በናንተ፡ ክፉት፡ ዝናም፡ ለዘር። ጠል፡ ለመከር፡ ተከልክሏልና፤

ወኢታንድዱ፡ መሥዋዕትየ፡ በከንቱ።

መሥዋዕቱን፡ በከንቱ፡ አት ሠዉት፤

ወኢይፈቅድ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፡ ወኢይትሜጦ፡ መሥዋዕተ፡ እምእዴክሙ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ መሥዋዕቱን፡ ወድጄ፡ ከእኛችሁ፡ አልቀበላችሁም፡ አላቸው፤

፲፩፤ እስመ፡ እምሥራቀ፡ ፀሐይ፡ እስከነ፡ ዓረብ፡ ይሴባሕ፡ ስምየ፡ በው ስተ፡ አሕዛብ።

ከፀሐይ፡ መውጫ፡ እስከ፡ ፀሐይ፡ መግቢያ፡ ድረስ፡ ስሜ፡ በአሕ ዛብ፡ ይመሰገናልና።

ወእምኵሉ፡ በሐውርት፡ ያመጽኡ፡ ዕጣነ፡ ለስምየ።

ከሀገሩ፡ ሁሉ፡ ለስሜ፡ መታ ሰቢያ፡ ሊሆን፡ ዕጣኑን፡ ያመጣሉ፤



ወመሥዋዕተ፡ ንጹሐ።

ንጹሑን፡መሥዋዕት፡ያመጣሉ፤

እስመ፡ ዓቢይ፡ ስምየ፡ በውስተ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ ስሜ፡ ገናና፡ ነው፡ ብሏልና፤

፲፪፤ አንትሙሰ፡ ታረኵስዎ።

የእግዚአብሔርን፡ ማዕድ፡ እና ንት፡ ታረክሱታላችሁ፡ ማለት፡ ዕውሩንም፡ አንካሳውንም፡ አይቀበልም፡ ትላላችሁ፤

እስመ፡ ትብሉ፡ ማዕደ፡ እግዚአብሔር፡ ንውር፡ ውእቱ።

የእግዚአብሔር፡ ማዕድ፡ አስነ ዋሪ፡ ነው፡ ትላላችሁ፤

ወእክሉሂ፡ ዘውስቴቱ፡ ምኑን፡ ውእቱ።

በፊቱ፡ የቀረበው፡ እህል፡ የተናቀ፡ ነው፡ ትላላችሁ፤ አባር፡ የመ ታውን፡ እህል፡ ከነእንክር ዳዱ፡ ታቀርባላችሁና፤

፲፫፤ ወትብሉ፡ ዝንቱኒ፡ እምእኩይ፡ ሕማም፡ ውእቱ።

ይህም፡ ከዓባር፡ የተነሣ፡ ነው፡ ትላላችሁ፤

ወነፋሕክምዎ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አድርጋችሁ፡ ሰበሰ

ባችሁትን፡ በረከት፡ አሳጣ ሁት፡ አለ፤

እስመ፡ ታበውዑ፡ ዘሄድክሙ፡ ሐን ካሰ፡ ወድውየ።

የቀማችሁትን፡ ዕውሩን፡ አንካ ሳውን፡ ታቀርባላችሁና፤ አን ድም፡ የቀማችሁትን፡ ዕውሩን፡ አንካሳውን፡ ወደምሥዋዑ፡ ታቀ ርባላችሁ፡ በአንዱ፡ ሁለት፡ ሦስት፡ ይለውጡበታልና።

ወእመሂ፡ አምጻእክሙ፡ መሥዋዕተ፡ ኢይትሜጠዎ፡ እምእዴክሙ፡ ይቤ፡ እግ ዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ መሥዋዕቱን፡ ብታመጡ፡ ከእ ጃችሁ፡ አልቀበልም አለ፤

፲፬፤ ርጉመ፡ ለይኩን፡ ኵሉ፡ ዘቦ፡ ተባዕት፡ ውስተ፡ መራዕይሁ።

ከመንጋው፡ ወንድ፡ ሳለ፡ እን ስት፡ የሚያቀርብ፡ የሚሠዋ፤

ወዘቦ፡ ብፅዓት፡ እንዘ፡ ይትከሃሎ፡ ዘይሠ ውዕ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘቦቱ፡ ነውር።

ስዕለት፡ ያለው፡ ለእግዚአብሔር፡ ደህናውን፡ መሥዋዕት፡ ማቅ ረብ፡ ሲቻለው፡ ነውር፡ ነቀፋ፡ ያለው፡ ዕውሩን። አንካሳውን፡ የሚያቀርብ፡ ሰው፡ ርጉም፡ ነው፤ ርጉም፡ ይሁን፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ፡ ዓቢይ፡ ንጉሥ፡ አነ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ገናና፡ ንጉሥ፡ ነኝ፡ አለ፤

ወይሰማዕ፡ ስምየ፡ በውስተ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፤

ስሜ፡ በአሕዛብ፡ ሁሉ፡ ይጠራል።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወይእዜኒ፡ ዛቲ፡ ትእዛዝ፡ ለክሙ፡ ለካህናት፤

ይች፡ ትእዛዝ፡ ለናንተ፡ ለካህናት፡ ናት፤

፪፤ ለእመ፡ ኢሰማዕክሙ፡ ወኢቦአ፡ ውስተ፡ ልብክሙ፡ ከመ፡ ተሀቡ፡ አኰቴተ፡ ለስምየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ይህን፡ ትእዛዝ፡ ባትሰሙ፡ ለስሜ፡ ምስጋና፡ ታቀርቡ፡ ዘንድ፡ በልቡናችሁ፡ ባያድር፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ወእፌኑ፡ ላዕሌክሙ፡ መርገመ፤

በናንተ፡ ላይ፡ መከራ፡ አመጣባችኋለሁ፤

ወእረግማ፡ ለበረከትክሙ፡ ወእመይጣ፡ ለበረከትክሙ፤

በረከትና፡ በረከት፡ አንድ፡ ወገን፡ ነው፤ በረከታችሁን፡ እለውጣታለሁ፤ አጠፋታለሁ፤

ወኢትሄሉ፡ እንከ፡ እምውስቴትክሙ፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ በናንት፡ ጸንታ፡ አትኖርም፤

እስመ፡ ኢትሔልዩዎ፡ በልብክሙ፤

በልቡናችሁ፡ አታስቡትምና፤

፫፤ ናሁ፡ አነ፡ እመይጥ፡ ዘባናቲክሙ፤

ዘባነ፡ ልቡናችሁን፡ እመልስዋለሁ፤

ወእዘሩ፡ ኃፍረተ፡ ውስተ፡ ገጽክሙ፤

በፊታችሁ፡ ኃፍረትን፡ አመጣባችኋለሁ፤

ወእሐሥር፡ በዓላቲክሙ፤

በዓለ፡ ሠዊትን፡ በዓለ፡ መፀለትን፡ አጠፋለሁ፤

ወእነሥአክሙ፡ ኅቡረ፤

አሥሩን፡ ነገድና፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ አንድ፡ አድርጌ፡ አስማርኬ፡ እሰዳቸዋለሁ፤

፬፤ ወተአምሩ፡ ከመ፡ አነ፡ ፈነውኩ፡ ለክሙ፡ ዘንተ፡ ትእዛዘ፤

ይኸንን፡ ዔዋዌ፡ እኔ፡ እንዳመጣሁባችሁ፡ ታውቃላችሁ፤

ከመ፡ የሀሉ፡ ሥርዓትየ፡ ኀበ፡ ሌዋውያን፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤ ሥርዓቴ፡ በሌዋውየን፡ ጸንቶ፡ ይኖራል፤



፭፤ ወይሄሉ፡ ሥርዓትየ፡ ዘሕይወት፡ ወዘሰላም፤

ሕይወት፡ ፍቅር፡ የሚገኝበት፡ ሥርዓቴ፡ ጸንቶ፡ ይኖራል፤

ወወሀብክዎሙ፡ ፍርሀተ፡ ይፍርሁ፡ ቅድመ፡ ገጹ፡ ለስምየ፤

ከስሜ፡ የተነሣ፡ ይፈሩ፡ ዘንድ፡ ፍርሀት፡ አሳደርሁባቸው፤

፮፤ ወይፈሁር፡ ሕገ፡ ጽድቅየ፡ ውስተ፡ አፉሁ፤

እውነተኛ፡ ሕጌ፡ በአንደበቱ፡ ጸንቶ፡ ይኖር፡ ዘንድ፤

ወኢይትረከብ፡ እንከ፡ ዓመፃ፡ ውስተ፡ ከናፍሪሁ፡ ዘእንበለ፡ ርትዕ፡ ወሰላም፤

ከእውነት፡ ነገር፤ ከፍቅር፡ አንድነት፡ በቀር፡ በዘሩ፡ባቤል፡ በከንፈሩ፡ ሐሰት፡ ነገር፡ አይነገርም፤ አንድም፡ ከኦሪት፡ ከወንጌል፡ በቀር፡ በጌታ፡ አንደበት፡ ሐሰት፡ አይነገርም፤

ወይሔሩር፡ ምስሌየ፤

ከኔ፡ ጋራ፡ በረድኤት፡ ይኖር፡ ዘንድ፤

ወለብዙኃን፡ ይሚጥሞሙ፡ እምጌጋዮሙ፤

ብዙዎች፡ ሰዎችን፡ ዘሩ፡ባቤል፡ መክሮ፡ አስተምሮ፡ ይመልሳቸው፡ ዘንድ፤ አንድም፡ ጌታ፡ [illegible]ምሮ፡

ከኃጢአት፡ ወደጽድቅ፡ ይመልሳቸው ዘንድ፤

፯፤ እስመ፡ ከናፍሪሁ፡ ለካህን፡ የዓቅብ፡ ምክረ፤

ጥንቱንም፡ የደግ፡ ካህን፡ ከንፈሮቹ፡ ሕግን፡ ይጠብቃሉና፤

ወየኃሥሥ፡ ሕገ፡ ጽድቅየ፡ ውስተ፡ ልቡ፤

እውነተኛ፡ ሕጌን፡ በልቡናው፡ ያስበዋል፤

እስመ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ውእቱ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብሔር፡ መልክተኛ፡ ነውና፤

፰፤ ወአንትሙሰ፡ ተግኅሥክሙ፡ እምፍኖቱ፤

እናንተ፡ ግን፡ ከሕጉ፡ ራቃችሁ፤

ወአስሐትክምዎሙ፡ ለብዙኃን፡ እምሕግ፤

ብዙዎቹን፡ ሰዎች፡ ከሕግ፡ ለያችኋቸው፤

ወአለውክሙ፡ ሥርዓተ፡ ሌዊ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ የሌዊን፡ ሥርዓት፡ አፈረሳችሁት፡ አለ፤

፱፤ ወአነሂ፡ ረሰይኩክሙ፡ ኅሡራነ፡ ወገዘርዋነ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፤

እኔም፡ በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ የተዋረዳችሁ፡ የተበተናችሁ፡ አደረግኋችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ፡ ኢዓቀብክሙ፡ ፍኖትየ፤

ሕጌን፡ አልጠበቃችሁምና፤

ወአድሎክሙ፡ ለገጽ፡ እምሕግየ፤

ከሕጌ፡ ይልቅ፡ ለሰው፡ ፊት፡ አደላችሁ፤

፲፤ አኮኑ፡ ፩ዱ፡ እግዚአብሔር፡ ዘፈጠረክሙ፤

የምታደሉለትንና፡ እናንተን፡ የፈጠራችሁ፡ አንድ፡ እግዚአብሔር፡ አይደለም? አንድም፡ የምታደሉበት፡ ደሀውንና፡ ባለጸጋውን፡ የፈጠረ፡ እግዚአብሔር፡ አይደለም?

ወአሐዱ፡ አቡክሙ፡ ለኵልክሙ፤

ለሁላችሁስ፡ አባታችሁ፡ አንድ፡ እግዚአብሔር፤ አይደለም?

ወኃደግሙ፡ ቢጸክሙ፤

አፍቅሮ፡ ቢጽን፡ ተዋችሁ፤

ወአርኰስክሙ፡ ሕገ፡ አምላክክሙ፤

የፈጣሪያችሁን፡ ሕግ፡ አፈረሳችሁ፤

፲፩፤ ወተኃድገ፡ ይሁዳ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ይሁዳ፡ በመከራ፡ ተጣለ፤

ወተመነነ፡ እስራኤል፡ በኢየሩሳሌም፤

እስራኤልም፡ በኢየሩሳሌም፡ ተናቀ፤

እስመ፡ ገመነ፡ ይሁዳ፡ መቅደስየ፤

ማደሪያዬ፡ ይሁዳ፡ በኃጢአት፡ ተዳድፏልና፤ አንድም፡ መቅደስ፡ ሰውነቱን፡ በኃጢአት፡ አሳድፏልና፤

ወዘአፍቀረ፡ ወዓጥአወ፤

በወደደው፡ በኃጢአት፤ በጣዖት፡ ሰውነቱን፡ አሳድፏልና፤

ወአምለከ፡ አማልክተ፡ ነኪር፤

የከነዓንን፡ ጣዖት፡ አምልኳልና፤

፲፪፤ ለይሥርዎ፡ እግዚአብሔር፡ ለኵሉ፡ ሰብእ፡ ዘይገብሮ፡ ለዝንቱ፡ ግብር፤

እንዲህ፡ ያለውን፡ ሥራ፡ የሚሠራውን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔር፡ ያጥፋው፤

ወይሕሥር፡ እምአብያተ፡ ያዕቆብ፤

ከያዕቆብ፡ ወገን፡ ተለይቶ፡ ይዋረድ፤

ወእምእለ፡ ያመጽኡ፡ መሥዋዕተ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ ለሚገዛ፡ ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕት፡ ከሚያመጡለት፡ ሰዎች፡ ተለይቶ፡ ይጥፋ፤

፲፫፤ ወዘንተ፡ ዘእጸልእ፡ አነ፡ ትገብሩ፤

እኔ፡ የምጠላውን፡ ይኸንን፡ ትሠራላችሁ፤

ወደፈንክምዎ፡ በአንብዕ፡ ለምሥዋዓ፡ እግዚአብሔር፤

አሥጠምክዎ፡ ሲል፡ ነው፡ ድኆችን፡ እየበደላችሁ፤

በብካይ፡ ወበገዓር፤

ድሆችን፡ እያስለቀሳችሁ፡ ድሆችን፡ እያስለቀሳችሁ፤



ወላህ፤

ድሆችን፡ እያሳዘናችሁ፡ ምሥዋዑን፡ በዕንብ፡ (በዕንባ) አሠጠማችሁት፤

ወዓዲ፡ ኢመፍትው፡ እንከሰ፡ እነጽር፡ መሥዋዕተክሙ፤

በዚህ፡ ላይ፡ ዳግመኛ፡ መሥዋዕታችሁን፡ በዓይነ፡ ምሕረት፡ እመለከተው፡ ዘንድ፡ አይገባም፤

ወእትመጌጦ፡ ኄረ፡ እምእዴክሙ፤

ከጃችሁ፡ በጐ፡ አድርጌ፡ እቀበለው፡ ዘንድ፡ አይገባም፤

፲፬፤ ወትብሉ፡ በእንተ፡ ምንት፤

አለመቀበልህ፡ ስለምን፡ ነው? ትሉኛ፡ እንደሆነ፤

እስመ፡ እግዚአብሔር፡ አስምዐ፡ ማዕከሌከ፡ ወማዕከለ፡ ብእሲትከ፡ እንተ፡ እምንዕስከ፤

በሕፃንነትህ፡ ባገባሃት፡ በሚስትህና፡ ባንተ፡ መካከል፡ እግዚአብሔር፡ አዳኝቶብሃልና፤

እንተ፡ ኀደጋ፡

በፈታሐት፤

ወይእቲ፡ ሱታፌከ፡ እንተ፡ በሕግ፡ አውሰብካ፡ ይእቲ፤

ይህችውም፡ ያገባኻት፡ አካልህ፡ መሰልኽ፡ ናት፤

፲፭፤ ወአኮ፡ ባዕድ፡ ዘገብሮ፡ ለዝንቱ፤

ይኸንን፡ ሙሴ፡ ያስተማረው፡

[illegible]

ወተረፈ፡ መንፈስ፤

ይኸውም፡ ልብ፡ ወለድ፡ ነው፡ እንጂ፤

ወትቤሉ፡ ምንተ፡ ይፈቅድ፡ እግዚአብሔር፡ ዘእንበለ፡ ዘርዕ፤

እግዚአብሔር፡ ብዝት፡ ወተባዝኍ፡ ከማለት፡ በቀር፡ ምን፡ ይሻል? ትላላችሁ፤

ወተአቀቡ፡ በመንፈስክሙ፤

እንዲህ፡ ከማለት፡ በልቡናችሁ፡ ተጠበቁ፤

ወኢትሕድግ፡ ብእሲተከ፡ እንተ፡ እምንዕስከ፤

በሕፃንነትህ፡ ያገባኻትን፡ ሚስትህን፡ አትፍታ፤

፲፮፤ ወእመሰ፡ ጸላዕካሃ፡ ፈንዋ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ብትጠላት፡ ግን፡ ፍታት፡ ስደዳት፡ ብሏል፡ ትላላችሁ፤

አምላከ፡ እስራኤል፡ ዘይትዌከፍ፡ ጸሎተ፡ ንጹሐን፡ በሕፅኑ፤

የእስራኤል፡ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር፡ የንጹሐንን፡ ጸሎት፡ በልቡናው፡ የሚቀበል፡ ነው፤

ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ተዓቀቡ፡ በመንፈስክሙ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ተጠበቁ፡ አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ወጓበይክሙ፡ ንዲገ፡ እስ፡ ታዓ
ዕዕዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ በነገርክሙ፤

በነገራችሁ፡ እግዚአብሔርን፡ የም
ታሳዝኑት፡ እናንተ፡ መፍታቱን፡
መተው፡ እምቢ፡ አላችሁ፤

ወትብሉ፡ በእንተ፡ ምንትኑ፡ አም
ዓዕናሁ?

እግዚአብሔርን፡ በምን፡ አሳዘ
ንነው? ትሉኛ፡ እንደሆነ፤

እስመ፡ ትብሉ፡ ኵሎ፡ ዘይገብር፡ እኩየ፡
ኢይዔድሞ፡ ለእግዚአብሔር፤

ክፉ፡ ሥራ፡ የሚሠራውን፡ ሰው፡
ሁሉ፡ እግዚአብሔር፡ ደስ፡ ኢያሰ
ኘውም፡ ትላላችሁና፤

ወኢያሀሙኒ፡ ኢይሠምር፤

እናንተ፡ ኃጢአቱን፤ መሥዋዕ
ቱን፡ የምትወዱ፡ ከሆነ፡ ሕዝ
ቡን፡ የምትከለክሏቸው፡ ከሆነ፤

አይቴኑ፡ እንከ፡ አምላከ፡ ጽድቅ፤

እውነተኛ፡ አምላክ፡ መሆኑ፡
ወዴት፡ አለ?

## ምዕራፍ ፫

### ጉባዔ

፩፤ ናሁ፡ አነ፡ እፌኑ፡ መልአኪየ፡
ዘይጸይሕ፡ ፍኖትየ፡ ቅድመ፡ ገጽከ፤

በፊትህ፡ ጎዳናዬን፡ የሚጠርግ፡
መልክተኛዬን፡ ሚልክያስን፡
እሰዳለሁ፤

ወይመጽእ፡ ግብተ፡ ውስተ፡ ጽርሑ፡
እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ መጥቶ፡ በኢየ
ሩሳሌም፤ አንድም፡ መልክተኛ፡
ቅዱስ፡ ገብርኤልን፡ እሰዳለሁ፤
ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ በማኅ
ፀነ፡ ማርያም፡ ያድራል፤

አንድም፡ ነቢሑ፡ ወእመኑ፡
ኢያለ የሚያስተምር፡ ዮሐንስን፡
እሰዳለሁ፤ ዮሐንስ፡ ባስተማራ
ቸው፡ ጌታ፡ ያድራል፤ አንድም፡
ሕግን፡ ሥርዓትን፡ የሚያስተ
ምር፡ መልክተኛዬ፡ ኤልያስን፡
እሰዳለሁ፤ ኤልያስ፡ ባስተማ
ራቸው፡ ጌታ፡ ያድራል፤

ዘአንትሙ፡ ተኃሥሡ፡ መልአከ፡ ሥር
ዓትየ፡ ዘአንትሙ፡ ትፈቅዱ፤

ዘአንትሙና፡ ዘአንትሙ፡ አንድ፡
ወገን፡ ነው፤ እናንተ፡ የምትሹት፡
የሥርዓቴን፡ መልክተኛ፡ ሚልክ
ያስን፡ እሰዳለሁ፤ አንድም፡ ዮሐ
ንስን፡ እሰዳለሁ፤

ናሁ፡ ይመጽእ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡
ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ይመጣል፡ አለ፤

፪፤ ወመኑ፡ ይትዔገሣ፡ ለመዓተ፡
ምጽዓቱ፤

መጥቶ፡ የሚያደርጋትን፡ መዓ
ቱን፡ የሚታገሣት፡ ማነው፤



ወመኑ፡ ይትቃወማ፡ ለእሳተ፡ ርእየቱ፤

አይቶ፡ የሚያመጣት፡ መከራ
ውን፡ የሚቀዋወማት፡ ማነው፤

እስመ፡ ለሊሁ፡ የሐውር፡ ከመ፡ እሳተ፡
ምንሀብ፤

እርሱ፡ እንደ፡ አጎዶ፡ (ወናፍ)
እሳት፡ በማስፈራት፡ ጸንቶ፡
ይኖራልና፤

ወከመ፡ እስ፡ የሐፅብ፤

የሚያጥቡ፡ ሰዎች፡ እንዲያጥቡ፤

ወያነብሩ፤

ሰዎች፡ አጥበው፡ እንዲያኖሩት፤

፫፤ ወይሰብክ፡ ወያጸሪ፡ ከመ፡ ብሩር፡
ወወርቅ፤

በመደሻ፡ መትቶ፡ እንዲሠራ፡
ወርቁን፡ ብሩን፡ እንዲያጠራ፤

ወይነጥፎሙ፡ ለደቂቀ፡ ሌዊ፤

ካህናትን፤ አንድም፡ ሐዋርያትን፡
በመከራ፡ አጥርቶ፤

ወይሰጠዎሙ፡ ከመ፡ ወርቅ፡ ወከመ፡
ብሩር፤

እንደወርቅ፡ እንደብር፡ በረድ
ኤት፡ ይቀበላቸዋል፤

ወይከውንዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ እለ፡ ያበ
ውዑ፡ መሥዋዕተ፡ በጽድቅ፤

ለእግዚአብሔር፡ መሥዋዕቱን፡
በውነት፡ የሚያቀርቡ፡ ይሆናሉ፤

፬፤ ወታሠምሮ፡ ለእግዚአብሔር፡
መሥዋዕተ፡ ይሁዳ፡ ወኢየሩሳሌም፤

የዐሥሩ፡ ነገድ፤ የሁለቱ፡ ነገድ፡
መሥዋዕት፡ እግዚአብሔርን፡
ደስ፡ ያሰኘዋል፤

በአምጣነ፡ መዋዕለ፡ ዓለም፤

እንደ፡ ዳዊት፤ እንደ፡ ሰሎሞን፡
ዘመን፤

ወበከመ፡ ዓመት፡ ዘቀዲሙ፤

እንደ፡ ሙሴ፡ እንደ፡ አሮን፡
ዘመን፡ ደስ፡ ታሰኘዋለች፤ አን
ድም፡ ወታሠምሮ፡ ብለህ፡
መልስ፤ የጌታ፡ መሥዋዕት፡ እግ
ዚአብሔር፡ አብን፡ ደስ፡ ታሰኘ
ዋለች፤ እንደ፡ መልከጼዴቅ፡
ዘመን፡ እንደ፡ አዳምና፡ እንደ
ሔዋን፡ ዘመን፡ ደስ፡ ታሰ
ኘዋለች፤

፭፤ ወእመጽእ፡ ኀቤክሙ፡ በፍትሕ፤

በፍርድ፡ ጊዜ፡ ወደናንተ፡ እመ
ጣለሁ፤

ወእኬንኖሙ፡ ለሰብእ፡ ሥራይ፤

ሥር፡ በሚምሱ፡ ቅጠል፡ በሚ
በጥሱ፡ ሰዎች፡ እፈርድባቸዋለሁ፤

ወለዘማውያን፤

በዘማውያንም፡ እፈርድ
ባቸዋለሁ፤

ወለሰማዕተ፡ ሐሰት፤

ሐሰት፡ በሚመሰክሩ፡ ሰዎች፡
እፈርድባቸዋለሁ፤

ወለእለ፡ ይምሕሉ፡ በስምየ፡ በሐሰት፤

ስሜን፡ ጠርተው፡ በሐሰት፡
በሚምሉ፡ ሰዎች፡ እፈር
ድባቸዋለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለእለ፡ የሐይድዎሙ፡ እስቦሙ፡ ለአሳብ፤

የምንደኞችን፡ የዕለት፡ ደመወዛቸውን፡ የሚቀሚቸውን፡ እፈርድባቸዋለሁ፤

ወለእለ፡ ይኰርዕዎሙ፡ ለዕቤራት፤

ባልቴቶችን፡ ራስ፡ ራሳቸውን፡ በሚመቷቸውም፡ እፈርድባቸዋለሁ፤

ወለእጓለ፡ ማውታ፤

እናት፡ አባቱ፡ ጥለውት፡ የሞቱትን፡ ራስ፡ ራሱን፡ የሚመቱትን፡ እፈርድባቸዋለሁ፤

ወለእለ፡ ይመይጡ፡ ፍትሐ፡ ፈላሲ፤

የመጻተኛውን፡ ፍርድ፡ በሚለውጡ፡ እፈርድባቸዋለሁ፤

ወለእለ ኢይፈርሁ፡ ስምየ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ስሜን፡ በማይፈሩ፡ ሰዎች፡ እፈርድባቸዋለሁ፡ አለ፤

፮፤ በከመ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክክሙ፡ ኢይትዌለጥ፤

ፈጣሪያችሁ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ እንዳልለወጥ፤

ከማሁ፡ አንትሙኒ፡ ደቂቀ፡ ያዕቆብ፡ ኢተኃድጉ፡ ዓመፃ፡ ዘአበዊክሙ፡ እለ፡ ዓለዉ፡ ሕግየ፡ ወኢዓቀብዎ፤

እናንተም፡ የያዕቆብ፡ ልጆች፡ ሕጌን፡ ያልጠበቁ፤ ሕጌን፡ ያፈረሱ፡ የአባቶቻችሁን፡ ኃጢ[illegible]

፯፤ ተመየጡ፡ ኀቤየ፡ ወእትመየጥ፡ ኀቤክሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በሕግ፡ ወደኔ፡ ተመለሱ፤ እኔም፡ ከመዓት፡ ወደምሕረት፡ እመለስላችኋለሁ፡ አለ፤

ወአንትሙሰ፡ ትብሉ፡ በምንት፡ ንትመየጥ፤

እናንተ፡ ግን፡ ወዴት፡ ሄደና፡ ተመለሱ፡ ትለናለህ፡ ትሉ ላችሁ፤

፰፤ የአቅዖኑ፡ ሰብእ፡ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ በሰው፡ ልደር፡ ቢል፡ ሰው፡ አትደርብኝ፡ ይለዋልን፤

ወናሁኬ፡ አንትሙ፡ አዕቀዕክሙኒ፤

እነሆ፡ እናንተ፡ እንዳላድርባችሁ፡ አደረጋችሁኝ፤

ወናሁ፡ ትብሉኒ፡ በምንት፡ አዕቀዕናከ፤

በምን፡ አትደርብን፡ አልንህ? ትሉኝ፡ እንደሆነ፤

አሥራቲክሙኒ፡ ወቀዳማያቲክሙኒ፡ ኀቤክሙ፡ ውእቱ፤

አሥራቱን፡ ቀደምያቱን፡ እስ[illegible]



፱፤ ወተዓውሮ፡ ተአወርክሙኒ፡ አንትሙ፤

እናንተ፡ ፈጽማችሁ፡ ቸል፡ አላችሁኝ፤

ወአዕቀዕክሙኒ፡ ኪያየ፤

እናንተም፡ አሰነካከላችሁኝ፡ ማለት፡ እንዳላድርባችሁ፡ አደረጋችሁኝ፤

ወዓመቲክሙኒ፡ ሐልቀ፤

ነግ፡ ሠልስት፡ እንመለሳለን፡ ስትሉ፡ ዘመኑ፡ ተፈጸመ፤

፲፤ ወአባዕክሙ፡ ኵሎ፡ ማዕረረክሙ፡ ውስተ፡ መዛግብቲክሙ፤

አዝመራችሁን፡ ሁሉ፡ ወደጎተራ፡ አገባችሁት፤

ወይከውን፡ በርበረ፡ ውስተ፡ ቤትክሙ፤

በቤታችሁ፡ ሳለ፡ ይበዘብዙታል፤

ሐልይዎኬ፡ ለዝንቱ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እስኪ፡ ይኸንን፡ አስቡት፡ አለ፤

ለእመ፡ ኢያርኃውኩ፡ ለክሙ፡ አስራበ፡ ሰማይ፤

ዝናም፡ ለዘር፤ ጠል፡ ለመከር፡ እኔ፡ ካልሰጠሁ፡ አይረባም፤ አይጠቅምም፤

ወእሰውጥ፡ ለክሙ፡ በረከትየ፡ እስከ፡ የአክለክሙ፤

ብትመለሱ፡ ግን፡ በረከቴን፡ እስ[illegible] ...ሁ፤

፲፩፤ ወእሁበክሙ፡ ሲሳየክሙ፤

ምግብ፡ ሲሆናችሁ፡ እሰጣችኋለሁ፤

ወኢያማስን፡ ለክሙ፡ ፍሬ፡ ምድርክሙ፤

አዝመራችሁን፡ አላጠፋባችሁም፤

ወኢየዓብር፡ ወይንክሙ፡ ዘውስተ፡ ገዳም፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በምድረ፡ በዳ፡ ያለ፡ ወይናችሁ፡ አይደርቅም፡ አለ፤

፲፪፤ ወያስተበፅዑክሙ፡ ኵሎሙ፡ አሕዛብ፤

አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ያደንቋችኋል፤

እስመ፡ ትከውኑ፡ አንትሙ፡ ከመ፡ ምድር፡ ሥምርት፡ በኀቤየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በኔ፡ ዘንድ፡ እንደለመለመች፡ ምድር፡ ትሆናላችሁ፡ ማለት፡ እንደ፡ አብርሃም፡ እንደሙሴ፡ ትሆናላችሁ፤

፲፫፤ አክበድክሙ፡ ላዕሌየ፡ ነገረክሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ በኔ፡ ላይ፡ ሐሜት፡ አጸናችሁብኝ፡ አለ፤

ወትብሉ፡ በምንትኑ፡ ሐመይናከ፤

ምን፡ ብለኸን፡ አማንህ፡ ትሉኝ፡ እንደሆነ፤

፲፬፤ እስመ፡ ትብሉ፡ ከንቱ፡ ዘተቀነይነ፡ ለእግዚአብሔር፤

ለእግዚአብሔር፡ የተገዛነው፡ መገዛት፡ ከንቱ፡ ነው፡ ትላላችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወምንትኬ፡ ረባሕነ፡ ዘዓቀብነ፡ ትእዛዞ፡ ለእግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔርን፡ ሕጉን፡ ትእዛዙን፡ የጠበቅን፡ እኛ፡ ምን፡ ተረባን፡ ምን፡ ተጠቀምን፡ ትላላችሁ፤

ናሁ፡ ተቀነይነ፧

እነሆ፡ ተገዛን፤ የተጠቀምነው፡ ምንድነው?

እስመ፡ ተቀነይነ፡ ቅድመ፡ እግዚአብሔር፡ ከንቶ፤

በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ከንቱ፡ መገዛትን፡ ተገዝተናልና፤

፲፭፤ ወናሁ፡ የሃም፡ ናስተብፅዕ፡ ባዕደ፤

እነሆ፡ ዛሬ፡ ጣዖቱን፡ እናመሰግናለን፤

ወየሐንፁ፡ ወይገብሩ፡ ስመ፤

ስማቸውን፡ የሚያስጠራ፡ ሥራ፡ ይሠራሉ፤

እስመ፡ ኮሎሙ፡ ይትቃወምዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወኢይድኅኑ፤

እግዚአብሔርን፡ ተቃውመውታልና፡ ሁሉም፡ አይድኑም፤

፲፮፤ ከመዝ፡ ሐመይዎ፡ እለ፡ ኢይፈርህዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ አሐዱ፡ አሐዱ፡ ምስለ፡ ካልኡ፤

እግዚአብሔርን፡ የማይፈሩ፡ ሰዎች፡ አንዱም፡ አንዱም፡ ካንዱ፡ ጋራ፡ እንዲህ፡ ብለው፡ አሙት፤

ወርእየ፡ እግዚአብሔር፡ ወሰምዐ፤

እግዚአብሔር፡ ሰምቶ፡ አየ፤

ወጸሐፈ፡ መጽሐፈ፡ ተዝካር፡ በቅድሜሁ፡ ለእለ፡ ይፈርህዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወለእለ፡ ኢይፈርሁ፡ ስሞ፤

የኃጢአታቸውም፤ የበጎነታቸውም፡ መታሰቢያ፡ ሊሆን፡ መጽሐፍ፡ ጻፈ፤ እግዚአብሔርን፡ ለማይፈሩ፡ ስሙንም፡ ለማይፈሩ፡ መታሰቢያ፡ ሊሆን፡ ጻፈ፤

፲፯፤ ወይከውኑኒ፡ ካህናትየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ አገልጋዮቼ፡ ይሆኑኛል፡ አለ፤

ለእመ፡ እገብር፡ አነ፡ ሕይወተ፤

እኔ፡ ሕይወትን፡ ብሰጥ፤

ወአኃርዮሙ፡ በከመ፡ ያበድር፡ ብእሲ፡ ወልዶ፡ ዘይትቀነይ፡ ሎቱ፤

ሰው፡ የሚገዛለትን፡ ልጁን፡ እንዲወድ፡ እወዳቸዋለሁ፤

፲፰፤ ወትትመየጡ፤

በሚጠት፡ ወደኔ፡ ትመለሳላችሁ፤

ወትሬእዩ፡ ማዕከለ፡ ጽድቅ፡ ወማዕከለ፡ ኃጢአት፤

በኃጢአትና፡ በጽድቅ፡ መካከል፤

ማዕከለ፡ ዘይትቀነይ፡ ወማዕከለ፡ ዘኢይትቀነይ፡ ለእግዚአብሔር፤

ለእግዚአብሔር፡ በሚገዛና፡ ለእግዚአብሔር፡ በማይገዛ፡ መካከል፡ የሚሆነውን፡ ታያላችሁ፡ ማለት፡ በጎ፡ ቢሠራ፡ ዋጋውን፤ ክፉ፡ ቢሠራ፡ ፍዳውን፡ ወቀ በሳልና፤



## ምዕራፍ ፬

፩፤ ወናሁ፡ ይመጽእ፡ መዋዕል፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ እንዘ፡ ይነድድ፡ ከመ፡ እሳት፤

በዚያ፡ ወራት፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ እንደሚነድ፡ እሳት፡ ሆኖ፡ ይመጣል፤

ወያውዕዮሙ፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ ወለኵሎሙ፡ ገበርተ፡ ዓመፃ፡ ከመ፡ ሐሠር፤

አሕዛብን፡ ሁሉ፡ ዓመፅን፡ የሚሠሩ፡ ሰዎችንም፡ ሁሉ፡ እንደ ገለባ፡ ያጠፋቸው፡ ዘንድ፤

ወታውዕዮሙ፡ ዕለት፡ እንተ፡ ትመጽእ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ የምትመጣ፡ ዕለተ፡ ዜዋዌ፡ ታጠፋቸዋለች፡ አለ፤

ወኢይተርፍ፡ ሥርዎሙ፤

አባትነታቸው፤

ወኢዓዕቆሙ፤

ልጆቻቸው፡ አይቀሩም፤

፪፤ ወይሠርቅ፡ ለክሙ፡ ለእለ፡ ትፈርሁ፡ ስምየ፡ ፀሐየ፡ ጽድቅ፤

ስሜን፡ ለምትወዱ፡ ለትሩፋን፡ ዘሩባቤል፡ ይወለድላችኋል፡ ኦሪት፡ ትሠራላችኋለች፤

ወሕይወት፡ ውስተ፡ ክነፊሁ፤

ከነቢያት፡ ከካህናት፡ ትምህርት፡ ትንቢት፡ ይገኛል፤ አንድም፡ [illegible] ፀሐይ፡

[illegible] ጽድቅ፡ ክር

ስቶስ፡ ይወለድላችኋል፤ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ከሱ፡ ይገኛል፤ አንድም፡ ከሐዋርያት፡ ልጅነት፡ ይገኛል፤ አንድም፡ ወንጌል ይገኛል፤

ወትወጽኡ፤

ከፋርስ፡ ወደኢየሩሳሌም፡ ትወጣላችሁ፤

ወታንፈርዕፁ፡ ከመ፡ ጣዕዋ፡ ዘተፈትሐ፡ እማዕሠሩ፤

ከማሠሪያው፡ እንደተፈታ፡ እንቦሳ፡ ትዘላላችሁ፡ ማለት፡ ደስ፡ ይላችኋል፤ አንድም፡ ከሲኦል፡ ወደ፡ ገነት፡ ትወጣላችሁ፡ ከማሠሪያው፡ እንደተፈታ፡ እንቦሳ፡ ደስ፡ ይላችኋል፤

፫፤ ወትከይድዎሙ፡ ለኃጥአን፤

በባቢሎን፡ ሰዎች፡ ትሰለጥኑባቸዋላችሁ፤ አንድም፡ በአጋንንት፡ ትሰለጥኑባቸዋላችሁ፤

ወይከውኑ፡ ከመ፡ ሐመድ፡ በታሕተ፡ እገሪክሙ፡ በዕለት፡ እንተ፡ ባቲ፡ እገብር፡ አነ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እኔ፡ ሚጠትን፡ በማደርግባት፡ ቀን፡ ከእግራችሁ፡ በታች፡ እንደትቢያ፡ ይሆናሉ፤ አንድም፡ ትንሣኤን፡ በማደርግበት፡ ቀን፡ አጋንንት፡ እንደ፡ አመድ፡ ይሆናሉ፡ ማለት፡ ይዋረዳሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፤ ወናሁ፡ አነ፡ እፌኑ፡ ለክሙ፡ ኤልያስሃ፡ ቴስብያዌ፡ ዘእንበለ፡ ትብጻሕ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ ዓባይ፡ እንተ፡ ታስተርኢ፣

እነሆ፡ እኔ፡ የምትገለጥ፡ ዕለተ፡ ምጽአት፡ ሳትደርስ፡ የቴስብያን፡ ሰው፡ ኤልያስን፡ እሰድላችኋለሁ፣ ቴስቢያዊ፡ ባለው፡ ቴዝቤጣዊ፡ ይላል፤

፮፤ ወይመይጥ፡ ልበ፡ አበው፡ ኀበ፡ ውሉድ፣

የለአብርሃምን፡ ሃይማኖት፡ ወደ ውሉድ፡ ይመልሳል፤

ወልበ፡ ብእሲ፡ ኀበ፡ ቢጹ፣

የውሉድን፡ ሃይማኖት፡ ወደ ትሩፋን፡ ይመልሳል፤ አንድም፡ እነሆ፡ ዮሐንስን፡ እሰድላችኋለሁ፡ የምትገለጥ፡ ዕለተ፡ ስቅለት፡ ሳትደርስ፡ የሐዋርያትን፡ አዕምሮ፡ ወደምእመናን፡ ይመልሳል፣ የምእመናንን፡ አእምሮ፡ ወደ፡ ጻድቃን፡ ይመልሳል፤

አመ፡ መጻእኩ፡ ወቀሠፍክዋ፡ ለምድር፣

መጥቼ፡ ይችን፡ ምድር፡ ባሳለፍኋት፡ ጊዜ፤

፬፤ ተዘከሩ፡ ሕገ፡ ሙሴ፡ ገብርየ፡ ዘአዘዝክዎ፡ በኮሬብ፡ ሥርዓተ፣

በኮሬብ፡ ያዘዝሁት፡ የሙሴን፡ ሥርዓት፡ አስቡ፣ ሥርዓተ፡ አምስቱን፡ መቶ፡ ሰባ፣ ወነበቦ፤


ወኵነኔ፡ ለኵሉ፡ እስራኤል፣

ለእስራኤል፡ የሠራሁትን፡ ዓሠርቱ፡ ቃላትን፡ አስቡ፤ አንድም፡ ሥርዓተ፡ ዘጠኙን፣ ወኵነኔ፡ ኢታምልክን፡ አስቡ፤ አንድም፡ ኦሪትን፣ ወንጌልን አስቡ፣ ተዘከሮሙ፡ ባለው፡ አማኅፀኖሙ፡ ይላል፤

አደራችሁን፡ ይዛችሁ፡ ተገኙ፤ አንድም፡ አደራ፡ አደራችሁን፡ ይዛችሁ፡ ተገኙ፡

ተፈጸመ፡ ዘ፲ቱወ፪ቱ፡ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ጸሎቶሙ፡ ወበረከቶሙ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፣ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር።

አነሣስቶ፡ ለአስጀመረን፣ አስጀምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፤ አሜን፡ በእውነት።



የብሉያት አንድምታ ትርጓሜ ሊቅ የነበሩት
መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ

www.ethiopianorthodox.org